## ታ ላ ቅ፡ የ ሰ ማ እ ታ ት፡ መ ታ ሰ ቢ ያ፡ ቀ ን፡ በ ኒ ዉ ዮ ር ክ፡ ከ ተ ማ፡

# በኢትዮጵያ ላይ ስለተፈጸመው የፋሺሽት የጦር ወንጀል ዓለም-አቀፍ ተቃውሞ

ፋሺሽት ኢጣልያ፤ በቫቲካን ድጋፍ፤ በ1928-33 ዓ/ም በኢትዮጵያ ላይ በተከለከለ የጋዝ መርዝና በዘመናዊ የጦር መሳሪያ እየታገዘች በፈጸመችው የጦር ወንጀል፤ አንድ ሚሊዮን ሕዝብ በመጨፍጨፉ እንዲሁም 2,000 ቤተ ክርስቲያኖችና 525,000 ቤቶች፤ ከነንብረቶቻቸውና ቅርሶቻቸው በማቃጠልና በተጨማሪም፤ በተፈጠረዉ የአካባቢ ብክለት ደግሞ 14 ሚሊዮን እንስሶች በመውደማቸው ሕዝባችን የደረሰበትን ረሀብና ሥቃይ መገመት አያዳግትም። ስለዚህ በየዓመቱ እንደሚደረገው፤ ዘንድሮም የየካቲት 12 የሰማእታት ቀንን ለማስታወስ በሰላማዊ ሰልፍና በመሳሰሉት ተቃውሟችንን በኢትዮጵያና በዓለም አቀፍ በሚገኙ 50 ልዩ ልዩ ከተሞች ለመግለጽ አቅደናል።

- ፋሺሽቶች፤ በሶስት ቀኖች ውስጥ፤ የካቲት 12-14 ቀኖች 1929 ዓ/ም፤ 30፣000 ኢትዮጵያውያንን አዲስ አበባ ላይ ጨፍጭፈዋል።
- ፋሺሽቶች በኢትዮጵያ ላይ ለፈጸሙት ግፍ የኢጣልያን መንግሥት ተገቢውን ካሣ አልከፈለችም።
- ከኢትዮጵያ ተዘርፎ በኢጣልያና በቫቲካን መንግሥቶች እጅ የሚገኘው መጠነ ሰፊ ንብረትም አልተመለሰም
- አይሑዶችን በመደጋገም ይቅርታ የጠየቀችው ቫቲካንም እስካሁን ድረስ የኢትዮጵያን ሕዝብ ተመሳሳይ ይቅርታ አልጠየቀችም። ኢጣልያ ሊቢያ ላይ ለፈጸመችው ወንጀል $5ቢሊዮን ዶላር የከፈለች መሆኑ የታወቀ ነው። በተጨማሪም ኬንያውያን በእንግሊዝ መንግሥት ለደረሰባቸው ግፍ ተገቢውን ይቅርታ ተጠይቀው ካሣ እንዲከፈላቸው አድርገዋል። የኢንዶኔዝያ ሕዝብም ከኔዘርላንድስ መንግሥት ተመሳሳይ ይቅርታ መጠየቅና ካሣ እንዲከፈል አድርጓል።
- የኢትዮጵያ ሕዝብስ መቼ ነው ከቫቲካንና ከኢጣልያ መንግሥቶች የሚገባውን ፍትሕ የሚያገኘው? ለክብራችንና ለመብታችን ካልታገልን ፍትሕ አይገኝም። “ባለቤት ካልጮኸ ጎረቤት አይረዳም” ነውና።

**በኒዉጀርሲ : በኒዮርክና፡ በኬኔቲኬት የምትኖሩ ኢትዮጵያዉያን ይህን በወገኖቻችን ላይ የደረሰዉን የግፍ ጭፍጨፋና እልቂት ለማሰብ ከዚህ በታች በተገለፀዉ ቀንና ቦታ ላይ እንድትገኙ ተጋብዛችኋል።**

**ቀን፡** Saturday, March 1st 2014
**ቦታ፡** 2 West 64th, New York, NY 10023
**ሰዓት፡** 1:00 PM to 4: 00 PM

**የዕለቱ ተጋባዥ እንግዶች፡,**

- **ዶ/ር ግርማ አበበ**
- **ዶ/ር ሥዩም ገ/እግዚአብሔር**
- **ሚ/ር ኒኮላ ዲማርኮ**

### ኢትዮጵያ መብትና ፍትሕ እንቁም። ኢትዮጵያ በነጻነት ለዘለዓለም ትኑር!

**ተባባሪ አዘጋጅ፡ የኒዉዮርክና አካባቢው የኢትዮጵያዉያን የጋራ መረዳጃ ማህበር**

Global Alliance for Justice – The Ethiopian Cause 4002 Blacksmith Drive, Garland, TX 75044, USA Tel: (214)703 9022 Email:info@globalallianceforethiopia.com